# እስከመቼ

ሰኔ ፲፱ - ሰኔ ፳፭ ቀን
፳፻፫ ዓ. ም. ቅፅ ፬ ቁጥር ፮
June 26 - July 2, 2011
Vol. IV, No. 6


# ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያዊነት

ዛሬ ኢትዮጵያዊያን በምናደርገው ትግል፣ ከልባችን አጥብቀን የያዝናቸውን መሠረታዊ እምነቶች፣ ደግመን ደጋግመን ማንሣት ብቻ ሣይሆን፣ ከፍ አድርገን በማስቀመጥ፣ በምንሰበሰብበት ጊዜ ብቻ ሣይሆን፣ በየቀኑም ብቻ ሣይሆን፣ በየሰዓቱ እንደምንተነፍሰው አየር መመርመርና ከሰውነታችን ማዋሃድ አለብን። ለዚህ ነው የዛሬዋ ***እስከመቼ*** ደግማ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያዊነት በማለት ማንሳት የምትፈልገው።

ኢትዮጵያዊያን ስንል፣ በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ነን ብለው የሚያምኑ፣ ይህ፣ ከኢትዮጵያዊ ቤተሰብ በመወለድ ወይንም ኢትዮጵያዊነትን በሕገ መንግሥቱ ውሳኔ መሠረት በመቀበል ይገኛል። ይህ ቀጥተኛና የማያሻማ ሃቅ ስለሆነ ግጭት አይጠበቅበትም።

እንግዲህ ጎዴም ተወለደ ሁመራ፣ ጋምቤላም ተወለደ አሳይታ፣ ሲወለድ ኢትዮጵያዊ ነው። በራስ የግል ውሳኔ ብቻ ነው ኢትዮጵያዊነት የሚሠረዘው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከኢትዮጵያዊ ቤተሰብ፣ ማለትም ቢያንስ ከአንድ ኢትዮጵያዊ ወላጅ የተወለደች፣ አውስትራሊያም ይሁን ሳዑዲ ዓረቢያ፣ አውሮፓም ይሁን አሜሪካ፣ ኢትዮጵያዊነት የማይነፈግ መብቷ ነው፣ አሁንም በፈቃዷ እስካልሠረዘችው ድረስ። በሌላ በኩል፣ የፖለቲካው ውጤት ሆና በስደት ለመሰንበት ያደረገችው የወረቀት ዜግነት፣ ኢትዮጵያዊነቷን አይነጥቃትም፣ መሠረዝ የምትችለው እርሷና እርሷ ብቻ ናትና፣ አንድም በፈቃዷ ሌላም ሆን ብላ በተግባሯ!

ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት ሁላችንም የምንለው አለን። ግማሾቻችን ልባችን ደውሎ፣ ጭንቅላታችን ቀምሮ፣ ከኛነታችን ጋር ቋጥረን የያዝነውን የግል ኢትዮጵያዊነት እናጠብቃለን። ሌሎቻችን ደግሞ በግል በግለሰብ የያዝነውንና ያመንበትን የሁላችን አስተሳሳሪ ገመድ አድርገን መውሰድ እንፈልጋለን። ቀሪዎቹ ደግሞ ሁሉን አቀፍ ቀመር ከመጽሐፍ አገላብጠን፣ ከፈላስፎች መርምረን፣ ከታሪክ አገላብጠንና ካለበት ፈልገን ኢትዮጵያዊነትን እናበጃለን።

ኢትዮጵያዊነት ***ለእስከመቼ፣*** ኢትዮጵያዊ መሆንን በመቀበል ይጀምራል። እንግዲህ ኢትዮጵያዊነት የማንነት አካል መሆኑ ነው። ማንነት ደግሞ ራስን ማወቅን ይጠይቃል። ከየት እንደመጡ ማወቅን ይጠይቃል። የታሪክንና የመልክዓ ምድር ግንዛቤን ይጠይቃል። ወደ የት እንደሚሄዱ፣ ራዕይንና ዕቅድን፣ በመሠረቱ ደግሞ የግለሰቡ የውስጥ ዕምነትና ለዕምነቱ መሠረት የሆነው የአመለካከቱ አናጭ መገመቻ ስርዓቱን ማወቅ ይጠይቃል።

ሌላው መጨመር ያለበት ደግሞ፣ ኢትዮጵያዊነት የትናንትን ተረክቦ፣ ዛሬ አዳብሮና አሳምሮ ለነገ ማስረከብ ነው። እንግዲህ በዚህ ወጣ በዚያ ወረደም፣ ይኸ የኢትዮጵያውዊያን በኢትዮጵያዊነታችን ለአትዮጵያዊነታችን የምናደርገው ትግል ነው። እናም ታሪካችንን ሌሎች ከፃፉት አናጣቅስም፣ ማንነታችንን ሌሎች ለኛ አይነግሩንንምና! ትግሉ በኢትዮጵያዊያን ሆኖ፣ በኢትዮጵያዊነታችንና ለኢትዮጵያዊነታችን ሆኖ፣ ከማን ጋር ማበር እንዳለብን ነጋሪ አንሻም! ሥልጣን ለመንጠቅ ከመጎምዠት በመነጨ የትግል መስመር፣ ከማንም ጋር አብሬ ከግቤ እደርሳለሁ እስካልተባለ ድረስ! ይኸ ደግሞ የኢትዮጵያዊያን የአንድነት ግባችን አይደለም፣ ከቋማጬ በስተቀር!

አሁንም ይኸ ***የኢትዮጵያውዊያን በኢትዮጵያዊነታችን ለአትዮጵያዊነታችን*** የምናደርገው ትግል ነው።


eske.meche@yahoo.com
ሒሊና ነጋሳ፣ ምክትል አዘጋጅ።